# በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ ላለፉት 15 ዓመታት የኢትዮጵያ ፕሬስ በርካታ ችግሮችን ተቋቁሞና ውጣ ውረዶችን አልፎ የተገመተውን ያህልም ባይሆን ተስፋ ሰጭ የሆነ እመርታ አሳይቷል። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የህዝብን ትኩረት የሳቡ በርካታ ጋዜጦችና መጽሔቶች በቅለው አብበዋል። አሁንም በማበብ ላይ የሚገኙ አሉ። ከዕለት ወደ ዕለት ለህትመት የሚበቁ ጋዜጦችና መጽሔቶች ቁጥር እየጨመረ እየሄደ ነው።

ያለፉት 15 ዓመታት ሂደት እንዳሳየው መንግሥት በህዝብ ዘንድ ተደማጭነትና ተወዳጅነት ያተረፈ የፕሬስ ውጤቶችንም ሆነ ጋዜጠኞች ውሃ ቀጠነ፣ ወንዝ ሽቅብ ፈሠሠ በሚል ዓይነት አጉል ምክንያት ሸንቁጧቸዋል። አንዳንዴም ፍዳቸውን አሳይቷቸዋል። ህልቁ መሣፍርት ችግሮችን ተቋቁመው የዳበሩና ያበቡ የፕሬስ ውጤቶችንም ለፍሬ ሣይበቁ አበባቸውን አርግፎታል። እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ውሎ እያደረ ይሻሻላል ሲባል ደግሞ በቅርቡ ያልታሰበና ያልታለመ አፋኝ ሕግ አርቅቆ በቂ ውይይት ሳይደረግበት እንዲያጸድቅ አድርጓል። ምርጫ 97 ባስከተለው ፖለቲካዊ ቀውስ ዋና ሰለባ የሆነው የግል ፕሬስ ካለፈው በተሻለ ሁኔታ እያንሠራራ ባለበት ወቅትና በርካታ ጋዜጦችና መጽሔቶች እየዳበሩና እያበቡ የጋዜጠኝነት ሙያና ሥነ ምግባርም የሚገባውን መልክና ቅርጽ እየያዘ ባለበት ወቅት የእንዲህ ዓይነቱ ሕግ መጽደቁ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን ለፕሬስ መዳበርና መጐልበት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቆርቋሪ የሆኑ ድርጅቶችንና ተቋማትንም ቅስም የሰበረ ነው።

"አዲሱ" የመገናኛ ብዙኀን እና የመረጃ ነፃነት ሕግ በጣት የሚቆጠሩ መሻሻሎችና አዎንታዊ ገጽታዎች ቢኖሩትም እንኳ በአንፃሩ ደግሞ የፕሬስ እና የመረጃ ነፃነትን በማያወላዳ መልኩ ከመሸበብ አልፎ ተርፎ ሕገ መንግሥቱን የሚቃረኑ አንቀጾችን ያካተተ ነው። ከኢ-ምንቱ ነገር ብንነሣ እንኳ ሕጉ የግሉን ፕሬስ በጠላትነት ፈርጆ የተነሣ ነው። ይህንን ለማለት የሚያስችለው በመግቢያው ላይ "መገናኛ ብዙኀን አሣጭ የሆኑትን ጨምሮ" የሚለው አገላለጽ ነው። ሕጉን ያረቀቀውና ያፀደቀው አካል "አሳጭ" ሲል ምን ለማለት እንደፈለገ ወይንም በሕጉ "አሳጭ" የሚለው ቃል ትርጉም ምን እንደሆነ ባይታወቅም እኛ እስከሚገባንና በህዝብ ዘንድ እንደሚታወቀው "አሳጭ" ማለት የሚያጋልጥ የተደበቀውን ለህዝብ በይፋ የሚያሣውቅ ማለት ነው። ሕጉ አሳጭ የሚለውን ቃል በአሉታዊ አንድምታ ቢያስቀምጠውም የግሉ ፕሬስ በኢትዮጵያ ምድር ብቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ መንግሥትና የመንግሥት አካላት፣ የግል ተቋማት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ

ድርጅቶችና ግለሰቦች በአይታወቅም፣ በአይሰማምና በአይታይም አስተሳሰብ የሚፈጽሟቸውን በደሎችና ስህተቶች ለህዝብ ሲያሳጣ ማለትም ሲያሳውቅና ሲያጋልጥ ኖሯል። የማሳጣቱ ተግባርና ሂደት፣ የነፃው ፕሬስ ዓላማና የጋዜጠኛ ተግባር ሆኖ ሳለ መንግሥት ግን እንደ እኩይ ተግባር በመቁጠር የግሉን ፕሬስና ጋዜጠኞቹን በጠላትነት ፈርጆ የእግር ብረት ሆኖ የሚያስረውን ሕግ አረቀቀለትና አፀደቀ።

የገንዘብ ምንጭ ዘጠና በመቶ ከሀገር ውስጥ እንዲሆን በማድረግ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የቀየደው መንግሥት በነካ እጁ የግሉን ፕሬስም ከሀገር ውጭ የሚመጣን ንዋይ እንዳይጠቀሙ ከልክሏል። እንደ ኢትዮጵያ ባለ ዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚ ችግር ባለበት ሀገር የኢኮኖሚ ልሂቃን መዋዕለ ንዋያቸውን ኢንቨስት ለማድረግ ፈራ ተባ በሚሉበት ብሎም በማይፈልጉበት፣ ህዝቡም ካለበት የኑሮ ጫና እና ውድነት አኳያ እንኳንስ ጋዜጣና ሌሎች የግል ፕሬስ ውጤቶችን ገዝቶ ማንበብና መጠቀም ይቅርና ለዕለት ጉርሱ የሚሆን ዳቦ መግዛት በተሳነበት ሀገር የፕሬስ ድርጅቶች በኩባንያ መልኩ ይቋቋሙ፣ ከሀገር ውጭ የሚመጣን መዋዕለ ንዋይ አይጠቀሙ ማለት ለዘላለም ባሉበት ሲዳክሩና በፋይናንስ አቅም ችግር ሲርመጠመጡ ይክረሙ ማለት ነው። ለመሆኑ መንግሥት ለራሱ ሲሆን፤ ቁጥር ስፍር የሌለው ንዋይ ከውጭ ሀገርና ከለጋሽ ድርጅቶች የሚበደርበትና የሚቀበልበት፤ በአንፃሩ ደግሞ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ድርጅቶችና ተቋማት፣ የግል ፕሬስ ድርጅቶችን ጨምሮ ብድርና እርዳታ የማይቀበሉበት ሚስጥር ምንድ ነው? የመንግሥት ፕሬሶችና ብሮድ ካስቲንግ ኤጀንሲዎች ከውጭ ሀገር ተቋማት የንዋይና የቁሣቁስ እርዋባን ቢቀርብላቸው አንቀበልም ይላሉ? እኛ እንደምንገነዘበው የአዲሱ የመገናኛ ብዙኀንና የመረጃ ነፃነት ጆሮ ዓይንና ቀልብ መሳብ የተሳናቸው የመንግሥት ፕሬሶችና ብሮደካስቲንግ ኤጀንሲዎች መንግሥት በሚመድብላቸው ግዙፍ ንዋይ በስርጭትና በሽፋን አድገው የመንግሥትን አቋምና አመለካከት ብቻ እንዲያስፋፉና በህዝብ ዘንድ እንዲያሰርጹ ማድረግና የግሉ ፕሬስ ደግሞ እየከሰመና በ1998 ዓ.ም. የደረሰበት ቁስል እያመረቀዘ እንዳይሞት እንዳይድን ሆኖ እንዲኖር ነው።

በተደጋጋሚ እንደሚሰማው በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የሕገ መንግሥቱ ጠበቃ ነኝ የዴሞክራሲ ፋና ወጊና መከታ ጋሻ ነኝ ይላል። እንዲህ እያለ እራሱን የሚፈርጅና የሕገ መንግሥቱ ጠበቃ ነኝ የሚል መንግሥት፣ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 29 አዲስ ባፀደቀው የመገናኛ ብዙኀንና የመረጃ ነፃነት ሕግ ሸሮታል ባይባልም ተቃርኖታል። የዴሞክራሲ ዋልታና ፋና ወጊ ነኝ የሚለው መንግሥት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋና መገለጫ የሆነውን ሃሳብን በነፃ የመግለጽና የፕሬስ መዳበር ጥበባዊና መሠሪ በሆነ ሕግ እየገታው ነው።

ከሁሉ የሚገርመው እና እንቆቅልሽ የሆነው ደግሞ በ1985 ዓ.ም. ታውጆ ሥራ ላይ የዋለውን ሕግ ለምን ማሻሻል እንዳስፈለገ አዲሱ ሕግ በመግቢያው ላይ ያተተው አንዳችም ነጥብ የለም። እንዲያውም በተቃራኒው መገናኛ ብዙኀን በነፃነት ለመንቀሳቀስ ይችሉ ዘንድ የቅድሚያ ምርመራ ገደብ እንዳይጣልባቸው ሕገመንግሥቱ ዋስትና የሰጠ መሆኑን በአጽንኦት በመገንዘብ በዜጎች መካከል በሚደረገው ነፃ የሃሳብና የመረጃ ልውውጥ እንዲሁም በመገናኛ ብዙኀን የአሠራር ነፃነት ላይ መሰናክል የነበሩ ተቋማዊ እና መዋቅራዊ ችግሮችን በማስወገድ በነፃ ሃሳብን የመግለጽና የመገናኛ ብዙኀንን ነፃነት አስመልክቶ ያዳበርናቸውን አወንታዊ እና ገንቢ ልምዶች የመጠበቅና ይበልጥ የማጠናከርን አስፈላጊነት በመረዳት በሚሉና ሌሎችም ውብና የተሽቆጠቆጡ ነጥቦች የተሞላ ነው። የ1985 ዓ.ምቱ ሕግ ምን ህጸጽና ጉድለት እንዳለበት የሚያሳይና የሚገልጽ ነጥብ ወይም ማብራሪያ የለም። እናም እንቆቅልሽ የሆነው "ለማዳበር" "መሰናክልና ችግሮችን ለማስወገድ" ወዘተ በሚል "ለማጠናከር" "መሰናክልና ችግሮችን ለማስወገድ" ወዘተ በሚል "ቅን" ሃሳብ ተነስቶ የበለጠ መሰናክልና ችግር የሚፈጥር ሕግ ማርቀቅና ማጽደቅ ነው።

ሕግ አርቅቆ በቅጽበታዊ ፍጥነት በማጽደቅ ረገድ በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት የሚስተካከለው የለም። የመገናኛ ብዙኀንና የመረጃ ነፃነት ሕግንም የሙያው ባለቤትና ባለድርሻ የሆኑ ወገኖችን አስተያየት ወደ ጐን በመተው አጽድቋል። የሕጉ መጽደቅና መተግበር የግል ፕሬሱን እድገት በመግታት ከሚያሳድረው አሉታዊ ተጽእኖ ባሻገር በሀገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና መልካም አስተዳደር መስፈን ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽእኖ መንግሥት አይረዳውም ማለት አይቻልም። በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በእውነት ለዴሞክራሲ ግንባታና ለመልካም አስተዳደር መስፈን የቆመ ከሆነ ባለሙያዎችና የፕሬስና የመገናኛ ብዙኀን ባለድርሻዎች የሰነዘሩትን ሂስና አስተያየት አጢኖ ሕጉን እንደገና ሊቃኘው የግድ ይላል። አሁን ባለበት ሁኔታና ይዘት ግን ሕጉ ከሕግነት ይልቅ የመመሪያነት ባህሪው ያመዝናል።

የግል ፕሬስ አባላትና ባለድርሻዎችም ሕጉን በተናጠል ከመኮነንና ከማውገዝ ይልቅ የጋራ መድረክ በመፍጠር ሕጉ እንዲሻሻል ብርቱ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህን ማድረግ የሙያ ግዴታቸው ብቻ ሳይሆን የሕልውናቸው ጉዳይ ነው። መንግሥትም ለባለሙያዎችና ለባለድርሻዎች አስተያየትና ሂስ ጆሮውን ማንቃት፣ ዓይኑን መክፈት፣ ልቦናውን (ሕሊናውን) ማዘጋጀት አለበት።